የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

☎ 55 35 06, 55 17 89, 12 39 00 - Fax 251-1-55 31 55 - ✉ 882
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ - Addis Ababa, Ethiopia

ቁጥር
Ref. No. 001/3/456/2002
ቀን
Date 25/03/2002

## ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ከገዥው ፓርቲና ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር የተደረገውን ድርድር በተመለከተ የተሰጠ መግለጫ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአለፉት ረጅም ዘመናት ሲታገልለት የኖረውን የሕዝብ ሥልጣን አመንጭነት፣ ባለቤትነትና ተቆጣጣሪነት መብት አጠናክሮ እንዲቀጥል ለማስቻል፣ ሕዝባችንም ለብዙ ጊዜ በመልካም አስተዳደር እጦት የተነሳ ብዙ ችግር ሲደርስበት የቆየ ሲሆን ይህን የመሰለ ፍትሕ የጎደለው አስተዳድር ለመታገልና ለማስተካከል የተቋቋመው የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ሕዝባዊ አላማውን ከግብ ለማድረስ ከፍተኛ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ቆይቷል አሁንም በማድረግ ላይ ይገኛል። ለዚህም አመራሩና አባላቱ እንዲሁም ደጋፊዎቹ ከፍተኛ መሥዋዕት ከፍለዋል።

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊ፣ በደል ነጻ ሆኖ ፍትሐዊና ከሙስና የፀዳ አስተዳደር እንዲያገኝ ለአለፉት 18 ዓመታት ሲታገል ቆይቷል። በመላው የአገሪቱ ክፍሎችም በመቶዎች የሚቆጠሩ ቢሮዎችን ከፍቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከጎኑ በማሰለፍ በጥንካሬና በቁርጠኝነት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

ይህን እንቅስቃሴ ያደርግ በነበረበት ወቅትም በአመራሮቹ፣አባላቱና ደጋፊዎቹ ላይ በፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ ከፍተኛ የሆነ የማሳደድ፣ የመደብደብ፣ የማሰርና የማሰቃየት ከዚያም ሲያልፍ የመግደል ድርጊት ሲፈጸምባቸው የነበረ ቢሆንም ይህን ችግር በመጋፈጥ የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴውን በማጧጧፍ ላይ ናቸው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከሐምሌ ወር 2001 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ በሚገኙ የታላላቅ አገሮች ኤምባሲዎች የሚመራው የኢትዮጵያ አጋር ድርጅቶች (Ethiopian Partners Group) ከገዥው ፓርቲ ጋር በአገሪቱ ፖለቲካዊ ችግሮች ላይ ሲወያዩ ከቆዩ በኋላ የ2002 ዓ.ም ብሔራዊ ምርጫ ሒደት ነጻና ፍትሐዊ እንዲሆንና በአለፈው እንደተፈጸመው ያለ አገርንና ሕዝብን የሚጎዳ ጥፋት እንዳይደገም በማሳሰብ ፓርቲያችን ከገዥው ፓርቲ አመራሮች ጋር በምርጫ ሥነ ምግባር ደንቦችና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ውይይት እንዲያደርግ ተጠየቀ።

ይህም ጥያቄ ከሰላማዊ ትግል ስትራተጂያችን ጋር ተጓዳኝ ስለሆነና ሕዝባችን የፈለገውንና ወደ አንድነት፣ ብልጽግና እና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በነጻነት ሊመራኝ ይችላል ብሎ ያመነበትን ፓርቲ መምረጥ ስለሚያስችለውና በአገሪቱም ዲሞክራሲን ለመገንባት መሠረት ሊያስጥል ያስችላል ብሎ ስለአመነ የመኢአድ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በድርድሩ ላይ ለመሳተፍ በሙሉ ድምጽ በመወሰን ፈቃደኝነቱን ስለአሳየ ሁለት ወር የፈጀው ድርድር በነሐሴ ወር 2002 ዓም እንዲካሄድ ተደርጓል።

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በድርድሩ ላይ እንዲካተቱለት ያቀረባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ብዙ ቢሆኑም ጥቂቶቹን ለሕዝባችን ለመግለጽ ያህል÷

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በፖለቲካ አመለካከቱ ብቻ ከመደበኛ ሥራው መፈናቀል፣ መደብደብ፣ መሳደድና በአጠቃላይ እለት ከእለት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕኖ እንዳይደረግበት መሰናክልም እንዳይፈጠርበት፣ ይህን አይነት ችግር ለመፍታትም ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በአባሎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ላይ በደል ደርሶብናል በማለት የሚያቀርቧቸው ቅሬታዎች በአስቸኳይ እንዲታረሙ፣

2. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፈለገውንና የመረጠውን የፖለቲካ ፓርቲ በመቀላቀል በነጻነት በአገሩ ላይ ፍትሐዊ አስተዳድር እንዲሰፍንና ዲሞክራሲን ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ላይ የበኩሉን አስተወጽኦ ማድረግ እንዲችል ሁሉም እንዲመቻችለት፣ይህም ሲባል አንድ የመንግሥት ሠራተኛም ሆነ ሌላ የፈለገውን የፖለቲካ ፓርቲ በመቀላቀሉ ወይም በመደገፉ የተነሳ ከእድገት እንዳይከለከል በሥራው ላይም ምንም ዓይነት ተጽዕኖ ወይም አድልኦ እንዳይደርስበት፣

3. የፕረስ ነጻነትም ለሰብአዊ መብት መከበር፣ ለዲሞክራሲ መጐልበት፣ ለሕግ የበላይነት እና ለአንድ ሕዝብ ሁለንተናዊ እድገት ያለውን ልዩ አስተዋጽኦ በመገንዘብ ለተፈጻሚነቱ ሁሉም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ እንዳለባቸው፣ በዚሁ መሠረትም ጋዜጠኞች በሙያዊ ሥራቸው ላይ በነጻነት በመሰማራት ያለምንም መዋከብና እንቅፋት ሳይጋረጥባቸው ተንቀሳቅሰው እንዲዘግቡ እድሉ እንዲሰጣቸው እንዲደረግ፣

4. ሦስቱ የመንግሥት አካላት ማለትም ሕግ አውጭው፣ ሕግ አስፈጻሚውና የዳኝነት አካላት የግልጽነት፣የታማኝነትና የተጠያቂነት ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለባቸው የተቀበሉና ለተግባራዊነቱም ቃል የገቡ እንዲሆኑ፣

5. የኢትዮጵያ የመከላከያ ሀይል፣ ተጠባባቂ ጦር እና የአካባቢ ታጣቂ ኃይል የአገራችንን ሕዝብ አንድነት ከወራሪ ኃይል ለመጠበቅና የአገራችንን ዳር ድንበር ለማስከበር የተደራጁ ኃይሎች መሆናቸውን በመገንዘብ በሕገ መንግሥቱ መሠረት ተግባራቸውን ከፖለቲካ ወገናዊነት ነጻ በሆነ አኳኋን እንዲያከናውኑ የሚሉትንና የመሳሰሉትን በማቅረብ ተቀባይነት እንዲኖራቸው የገኘው ፓርቲም ለእነዚህና ሌሎች በተፈረመው ሰነድ ላይ በመካተት የቀረቡትን ጉዳዮች ተግባራዊ ለማድረግ በቁርጠኝነት ቃል ገብቷል።

6. ምርጫው ከአድልኦ በጸዳ ሁኔታ መካሔድ ይችል ዘንድ ፓርቲዎች ምክር ቤት አቋቁመው ይህን ሁኔታ እንዲከታተሉና ሕገ መንግሥቱን ያከበረ እንዲሆን ሥልጣን የተሰጣቸው መሆኑ፣

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፣

አንተም እስካሁን ድረስ ስትደማለትና ስትሞትለት የነበረው ጥያቄ ከዚህ ያለፈ እንዳልነበር በመገንዘብ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ድምጽህን ይዞ በመደራደር አንተን ባለድል በማድረጉ ደስታውን ካንተ ጋር ይጋራል፡፡

አንዳንድ የሰላማዊ ትግልን አስፈላጊነትና ውስብስብነት በጥልቀት ያልተረዱ ጥቂት ድምጻዊ ወገኖች የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በድርድሩ ላይ መሳተፉና ከገዥው ፓርቲ አመራሮች ጋርም ስምምነት መደረሱ እንዳላስደሰታቸው ሲገልጹ ይሰማል:: ከሰላማዊ ትግል መሠረታዊ መርሆዎች መካከል በአገራዊ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በግልጽነትና በእውነተኛነት ላይ በመመርኮዝ መወያየትና መደራደር፣ የልዩነቶችን ስፋት በማጥበብ በሰፊው መመካከር፣ ልዩነቶችን በማቻቻል ቅራኔዎችን በሥር ነቀልነት ለመፍታት መጣር ነው:: የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅትም የኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን መብቶች በሚያስጠብቅና በሚያስከብር ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ ድርድሩን አካሒዷል፡፡ ከድርደሩም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ ድል እንዳስገኘን እናምናለን፡፡ መኢአድ አሁንም ሆነ ወደፊት የፖለቲካ አቋሙን በምንም አይነት አይለውጥም ለማንም አሳልፎ አይሰጥም፡፡ ለታሪክና ለትውልድ ፋይዳ ለሌለውና ለጊዜያዊ የፖለቲካ ፍጆታና ተወዳጅነት ብቻ ሲልም አይሰራም፡፡ ከገዥው ፓርቲ ጋር በምርጫ ሥነ ምግባር ደንቦችና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ መደራደር ማለት ከኢህአዴግ ጋር የዓላማም ሆነ የፕሮገራም አንድነት መፍጠር ማለት አይደለም ስለዚህ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ካለፈው ታሪካችንና አሁንም ቢሆን አገራችን ካለችበት አስቸጋሪ የፖለቲካ፣ የኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴ አኳያ ነገሮችን በጥሞና፣ በጥልቀትና በማመዛዘን እንዲመለከቱት ልናሳስብ እንወዳለን፡፡

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ ካደረገው ድርድር ለሕዝባችንና ለአገራችን ካስገኛቸው መሰረታዊ ጥቅሞች መካከል ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህልም፡-

ሀ. ከ1997ቱ ብሔራዊ ምርጫ ውጤት በኋላ ወደ ፓርላማ ከመግባቱ በፊት ቅንጅት መሟላት አለባቸው በማለት በቀዳሚነት አቅርቧቸው የነበሩ ስምንት ጥያቄዎች ዛሬ ምላሽ አግኝተዋል

ለ. ከ1997 ዓ.ም ብሔራዊ ምርጫ ጋር በተዛመደ ምክንያት እስከአሁን ድረስ ታስረው በመማቀቅ ላይ ያሉ ኢትዮጵያውያን ሁኔታው ተመርምሮ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በነጻ ይለቀቃሉ፣ በተመሳሳይ ምክንያት ክስ ተመስርቶባቸው ጉዳያቸው በሒደት ላይ የነበር አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችንም የክሱ ሁኔታ ተጣርቶ ይሰረዝላቸዋል፣ አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን እንዲሁም ሌሎች በፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ በማንኛውም የመንግሥትም ሆነ የፓርቲ ኃላፊዎች ምንም ዓይነት በደል አይፈጸምባቸውም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብም በሚቀጥለው ግንቦት 2002 ዓ.ም በሚደረገው ብሔራዊ ምርጫ ላይ በነጻነት የፈለገውን የፖለቲካ ፓርቲ እንዲያስተዳድረው የመምረጥ መብቱ እንዲረጋገጥለት መሠረት ተጥሏል:: በአጠቃላይ በድርድሩ የተካተቱና ከስምምነት ላይ

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት "መኢአድ"
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY (AEUP)

የተደረሰባቸው አበይት ጉዳዮች በአገራችን የዲሞክራሲን መሠረት ለመጣል እንደሚያስችሉ ታምኖባቸዋል፡፡

በምርጫ ቦርድና አሠራሩ ዙሪያ የነበሩ ችግሮችን በመመርመር እንዲስተካከሉ እንደሚደረግ መግባባት ላይ ተደርሷል፣ ስለዚህ ነጻ ምርጫ ለነጻ ሕዝብ!

ስለዚህ ሕዝባችን በጥልቀትና በጥሞና እንዲረዳልን የምንፈልገው የመላው ኢትዮድያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የኢትዮድያን አንድነት፣ ሉዓላዊነትና ክብር ለማስጠበቅ፣ ሁሉም ኢትዮጵያውያዊ ፍትሐዊ የሆነ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ አስተዳድር እንዲያገኝ አስፈላጊውን ጥረት ከማድረግ ባሻገር የአገሪቱንም ሆነ የሕዝቧን ብሔራዊ ጥቅም ለማንም ሆነ በማንኛውም መንገድ አሳልፎ በመስጠት ያልተደራደረና ወደፊትም የማይደራደር መሆኑን ተገንዝቦ በሚቀጥለው ግንቦት 2002 ዓ.ም ለሚደረገው ብሔራዊ ምርጫ በመካሔድ ላይ ባለው ዝግጅት ከወዲሁ ራሱን መርምሮ ከመኢአድ ጎን በመሰለፍ የበኩሉን አስተወጽኦ እንዲያበረክት የመላው ኢትዮድያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የክብር ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

**መኢአድ ባለበት ሁሉ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት አለ!!**

የመላው ኢትዮድያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ)

ህዳር 2002 ዓ.ም

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት "መኢአድ"
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY (AEUP)